# የዓለም ማህበረሰብ ለኢትዮጵያ ትኩረት ሠጠ
# የለዉጡ ማዕበል የመጨረሻዉ ምዕራፍ ደረሰ

March 26, 2018

ዳንኤል ጎበዜ

አገራችን ኢትዮጵያ በትግራይ ነጻ አዉጭ ግንባር ቁጥጥር ስር ከወደቀችበት ጀምሮ በዉስጥም በዉጭም በዜጎች ላይ የአፈና ዘመቻ ለ 27 ዓመታት ያህል ተካሂዷል፤ የአገሪቱን አንጡራ ሃብት እያጋበሱ የአካባቢ መሬወችን በዓለም አቀፍ ደረጃ በገንዘብ እዬደለሉ ኢትዮጵያዊያንን አጥቅተዋል/ ለሞት ዳርገዋል፤ ጩኸታቸዉ በየዲፕሎማሲዉ ማህረሰብ እንዳይሰማ በአጎራባች አገር ተሰደዉ እንኳ እንዳይቀመጡ ነብሰ ገዳዮችን አሰማርተዉ ሲያሳዱ ቆይተዋል፤ አሁንም ሥደቱ፤ በርሃብ መጠበሱ ቀጥሏል፤ 16 ሚሊዮን የተራቡ ወገኖቻችን ድረሱልን እያሉ ነዉ።



ባለፉት ሶስት ዓመታት የህዝባዊ ማዕበሉ ያለማቋረጥ ወያኔን በማንቀጥቀጡ ሁኔታወች በፍጥነት እዬተቀያዬሩ ለዓለም ማህበረሰብ አነጋጋሪ እዬነ ወያኔ እየ መከነ የትግሉ ትኩሳት እጨመረ እዉቅናን እያገኘ መቷል። በዙሪያችን ያሉ መንግስታትና ህዝቦችም ግፉና ጭቆናዉ ከመጠን አልፉ ለዉጭ እዬተረፈ በመሆኑ ወያኔ የአካባቢዉን ቀጠና ሊያመሰቃቅል ነዉ በሚል ስጋት አምባ ገነን መንግስት ነዉ ማለት ጀምረዋል። ከወያኔ የዉሸት ወዳጅነት እዬወጡ ከተበላሸ ሥርዓት ወዳጂነት እዬሸሹ አጋርነታቸዉን ለኢትዮጵያ ህዝብ መግለጽ እዬሞከሩ ነዉ፤ ይህ አቋም የሚያኮራ ደስ የሚያሰኝ ነዉ። ለአፍሪካ ትልቅ ዉለታ ለሰራ ለነጻነት፤ለፍትህ፤ ለዲሞክራሲ እና የህግ የበላይነትን እዉን ለማድረግ ለሚታገለዉ የኢትዮጵያ ህዝብ መደገፍ ተገቢ

ምላሽም ነዉ። ያለዉ ተጨባጭ ሁኔታ የሚያሳየዉ ወያኔ ህዝባዊነት የሌለዉ አገዛዝ መሆኑ እየተጋለጠ እስካሁን በተጭበረበረ ዲፕሎማሲ መቆየት የማይመች እዬሆነ መቶባቸዋል፤ ቢያንስ አብዛኛዉ አጎራባች ማህበረስብ ከአገሩን የዲሞክራሲ ትግል ታሪክ ጋር አነጻጽሮ የድጋፍ ድምጽ እያሰማ ነዉ።

ከ27 ዓመታት የግፍ አገዛዝ በኋ የትግራይ ነጻ አዉጭ ግንባር ህዝቡን እጨፈጨፈ ዘረኛ መንግስት ሁኖ መቆዬቱ ከጊዜ ወደጊዜ እዬተከሰተላቸዉ ይህ የጥፋት መንገድ ለመላዉ አፍሪካ አደገኛ እንደሆነ አጎራባች አፍሪካዊያን ትምህርት ቀስመዋል። በእርግጥም በአሁኑ ፈታኝ ሰዓት ከጎናችን መቆም ይገባቸዋል። ኢትዮጵያን የሚያዉቋት በነጻነት አራያነት ነዉ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዳር ድንበሩን ለማስከበር ከቅኝ ገዥ ወራሪወች ጋር ተፋልሞ፤ ደሙን አፍሶ፤ አጥንቱን ከስክሶ ነጻ የሆነ ህዝብ ብቻ ሳዕሆን የአፍሪካ ህዝቦች ከቅኝ ገዥወች ነጻነትን የማግኘት ትግል ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደረገ ህዝብ ነዉ።

በአገራችን ታሪክ ፤የኢትዮጵያ ህዝብ ከጥንት ዘመን ጀምሮ በሽምግልና/በገዳ አስተዳደር፤ በሃይማኖት የእርቅ አፈታት ብዙ የተነገረለት ህዝብ ለመሆኑ የታሪክ ማስረጃወች አሉ፤ ሊቃወንት ይመሰክራሉ፤ በመጽሃፍ ቅዱስ፤ከቁራን እስከ ድርሳናት ተነበዋል። ይህን የረዥም ዘመን የመልካም ባህል ተመክሮ የመላዉ አፍሪካ አካል የሆነዉን ታሪክ ጎረቤት ወዳጆቻችን ጠንቅቀዉ ያዉቃሉ። በመቻቻል እራሱን ሲመራ የቆዬ አሁንም ሊመራ የሚችልን እንግዳ ተቀባይ ህዝብ በግፍ ደምም መታጠቡን በማየታቸዉ ከወያኔ የዲፕሎማሲ እስር ቤት ሹልክ እያሉ በመዉጣት ላይ ናቸዉ። እጅግ ጥሩ ነዉ፤ ፤ እሰዬዉ ያሰኛል። ይህ አፋኝ አምባ ገነን እንደማይቆይ አዉቀዉታል ማለት ነዉ፤ እኛም አዉቀናል፤ ታላቅ ባለታሪክከሆነዉ ህዝብጋርበመቆማቸዉሊመሰገኑይገባቸዋል።

ይኸዉና ወገኖቸ፤ ወያኔ ከመጣ ጀምሮ የባህል ፤ የሽምግልና፤ የአባገዳዎች ሌሎችን ለቅራኒ አፈታት የምንጠቀምባቸዉ እሴቶቻችን በማጣጣል፤ በመናቅ እዬረገጡ፤ እያበላሹ፤የሃይማኖት አባቶችን ወደሰይጣንነት ቀይረዉ ለህዝብ እንዳይቆሙ በዘር ያቧደኑ በቀልተኞች ናቸዉ። በወያኔ የተደራጁ ጳጳሳት ጭምር የክህደት ስራ እዬሰሩ ለሆዳቸዉ ብቻ እያደሩ ጀሮ ዳባ ልበስ ብለዉ መኖሩን የመረጡ ሁነዋል። በዚህ ጉግ ማንጉግ የጨለማዉ ዓመታት የግዛት ዘመን የሃይማኖት አባት፤ ሽማግሌ ጠፍቶ ሁሉም ከወያኔ የተጠጉ ሆዳሞች ሁሉ እንደ ወያኔዎች ጨካኞች ናቸዉ። ለህጻናት፤ ለአዛዉንት፤ ለወጣት ደም መፍሰስ ደንታ የሌላቸዉ መስቀሉን የካዱ ቀሳዉስት ሆኑዉ ከርመዋል። እጅግ ያማል። አጎራባች አገሮች ይህንን ሁሉ ታዝበዉ ዘግበዉ ፤በምሁራን አስገምግመዉ በሚያስገርም ሁኔታ አሁን ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር መቆም ተገቢ ነዉ ብለዉ እዬወሰኑ ነዉ። ዋና ምክንታ ለራሳቸዉ ሰላምና፤ብልጽግና ወሳኝና የሰብአዊነት ጥያቄ መሆኑን በማመናቸዉ ነዉ። በዚህ በኩል አሜሪካ፤ አዉሮፓ መሪ ሚና እዬተጫወቱ በመሆኑ እጅ ደስ ሊለን ይገባል። በተለይ 10 ሚሊዮን ለጠፋዉ አማራና ኦሮሞ መርፌ ተወግቶ እንዳይወልድ በማምከንና በግድያ ላለቀዉ የዘር ማጥፋት ወንጀል በዓለም ፍርድ ቤት የመክሰስ ጉዳይ ላይ እንዲተባበሩን የበለጠ ድጋፋቸዉን እንጠይቃለን። ነገር ግን ለፋታም መዘንጋት የሌለበት ቁም ነገር፤ የማታ ማታ ወሳኙ የኛ የኢትዮጵያዉያን ቆራጥ የተባበረ አንድነትን የተላበሰ ትግል ነዉ። ወዳጆቻችን ድል ስናደርግ እንኳን ደስ ያላችሁ ለማለት ዝግጁ ናቸዉ፤ ህዝብ ፈቅዶ ለመረጠዉ መንግስት የእርዳታ እጃቸዉን ለመዘርጋትም የሚያግዳቸዉ የለም።

ወደ መጨረሻየ ልምጣና አንድ የጥገና ለዉጥ ጉዳይ ላንሳ፤ አቶ ኤርሚያስ ለገሰን በአገላለጽ ችሎታዉ አከብራለዉ በጥገና ለዉጥ አካሄዱ ግን የላላ አቋም ነዉ የሚል እምነት አለኝ፤ በኢሳት ላይ የትንታኔ አቀራረብ ላይ የሰነዘረዉን ሃሳብ ቀንጨፍ ላድርግ። በኢሳት ዉይይት አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስተር እንዲፈጽም የጠየቀዉን አምስት ጥያቄ እኔም እጋራለሁ፤ ጥያቄዉ ቁልፍና ጥሩ የምንመኘዉን ያካተተ ጥያቄ ነዉ እኔም ምኞቴ ነበር። ነገር ግን በወያኔ የተሰየመ አዲስ ሹም ሊፈጽመዉ ሊያስፈጽመዉም ፍጹም አይችልም። እንዲያዉም አጉል ከአበደ ዉሻ ጋር ትግል ማጋጠም እንደማለት ነዉ። የተለከፈ ዉሻ በቅጽበት መወገድ እንጂ በሰፈር አካባቢ ከቆ በልክፍት ሁሉን ያዳርሰዋል፤ ተስፋ የሌለዉ ጭዋታ ነዉ። በመዋቅሩ የተዘረጋዉ ተንኮል አሁንም ማቆሚዉ የሌለዉ የዘር መርዙ ቀላል አይደለም። ለይቅርታ እንኳን ጭራሽ ቦታ የሌለዉ ቡድን ነዉ።

እሺ፤ አዲሱ ሹም አስቸኳ ጊዜ አዋጁን ያንሳ!፤ ወንጀለኞችን አሰርኩ ይበል፤ ነብሰ ገዳዮችን ማለቴ ነዉ። ወያኔ ሁኖ እኮ ያልገደለ ያላስገደለ የሌም። አስቸኳ ጊዜ አዋጁ አሁን ተደጋግሞ ይፋ ሆኖ በአዋጅ ታጀቦ መጣ ኢንጂ የኢትዮጵያ ህዝብ ለ 27 ዓመታት በመሳሪያ አፈሙዝ ስር ገዝተዉታል።አዋጁ ቢነሳም በጓሮ በር መተዉ ያፍናሉ ፤ይገላሉ፤ ቤት ያፈርሳሉ በጉልበት ነጥቀዉ የወሰዱትን መሬት በሰፊዉ ከመዝረፍ አያቆሙም። በአሁኑ ሰዓት እንኳን ሥብሰባ ላይ ተቀምጠዉ ህዝብ

በማስጨፍጨፍ በዘረፋ ላይ ተሰማርተዋል ። አራሹን ገበሬ በቦረና/ሞያሌ ፤በጎንደር፤ በጎጃም ፤በወለጋ እያሳፈኑ ነዉ፤ የሙብት ታጋይ የፍትህ እና የአንድነት አቀንቃኞች እነ ስዩም ተሾመ፤ እነታዬ ደንደኣን አፍነዉ ወስደዋል። በዚህም አያቆሙም፤ የህዝብ ወገን የሆኑቱን አድብተዉ ለመጉዳት ለመጨረስ የተዘጋጁ መሆናቸዉን የኢትዮጵያ ህዝብ አዉቆ እራሱን በመከላከል እና ከማጥቃት ዉጭ ሌላ ምርጫ የለዉም። ይህ የማይሸራረፍ በዚህ ዘመን የገጠመን መወጣት ያለብን አገራዊ ግዴታ ነዉ።

ወደጥገናዉ ልመለስና አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስቴር የሚያመጣዉ ችግር ይኖራል የሚል ስጋት ያላቸዉ ጥቂት አይደሉም። ይህም አይዟችሁ የጥገናዉ ጊዜ ስለሚወስድ ነዉ እያሉ ትግሉን ያቀዘቅዛል የሚል ጨዋታ ነዉ። ይህም እዉነትነት ያለዉ የስጋት ጥርጣሬ ነዉ። ትግሉ ተዘናግቶ ቀዝቀዝ ሲል ወያኔ አገግሞ ይነሳና የእርስ በእርስ ግጭቱን ይቀጥላል፤ የነጻነት ቀን እጅግ ይራዘማል፤ ቀስ በቀስ አዲሱን ጠቅላይ ሚኒስተር በኢህአዴግ ስም የተጻፈ መግለጫ ከማንበብ ዉጭ በመረጃ የተደገፋ አመራር ሊሰጥ አይችልም።

ኢህአዴግ በተባለ መንደር ከእንግዲህ አስተዳደር አቁሟል። ሁላችንም እርማችን እናዉጣ። የወያኔ ዉስብስብ ችግር ሊወገድ የሚችለዉ በአገሪቱ ሰላምና መረጋጋት የሚገኘዉ የህዝብ አሜነታን ያገኘ ሁሉን ያሳተፍ የሽግግር መንግስት ሲቋቋም ብቻ ነዉ። ህዝብ ላይ ወንጀል የፈጸሙሙ ወደ እዉነተኛ ፍትሃዊ ፍርድ የሚቀርበዉም ለህዝብ የቆመ ስርዓት ባለበት አገር ነዉ። እነሱ በሾሙት ጠቅላይ ሚኒስተር ከጦርነት ፤ ከአፈና ፤ከስርቆት ዉጭ የሚፈጸም አገራዊ ጉዳይ አይኖርም። ዜጎች እየታሰሩ መሰቃየታቸዉ ጭራሽ አይቆምም። በወያኔ ባህል አስሮ ቶርች ማድረግ እና ስብዕናን የመንካት አባዜ ሱሳቸዉ ነዉ።

ሌላዉ የዘር ፖለቲካ የህልዉናቸዉ መሰረት በመሆኑ የሚፈታዉ አዲስ ሥራት ብቻ ነዉ። የአፍሪካ አገሮች ይህን የዘር በሽታ ለማስወገድ እዬሰሩበት ነዉ። አሁን ስለኢትዮጵያ ህዝብ ጭፍጨፋና ጭቆና መናገር መጀመራቸዉ ድንገት የመጣ አይደለም ፤ይልቁንስ በዉስጣቸዉ ቋጥረዉት ለአመታት የቆዩት ጊዜዉን ጠብቆ የመጣት የህዝቦች አንድነት ትግል ዉጤት ነዉ።

ጥያቂያችን/መልክታችን

1 መሳሪያ ለማስፈታት የሚካሄደዉ የአፈና ዘመቻ በአስቸኳይ ይቁም

2 ለህዝባቸዉ የቆሙ እዉነት በመናገራቸዉ የታሰሩ አቶ ሥዩም ተሾመና አቶ ታዬ ደንደአ በአስቸኳይ ይፈቱ

3 ህዝብ ሙሉ በሙሉ የተቃወመዉ ወታደራዊ አዋጅ በፍጥነት ይነሳ

4 የትግራይ ነጻ አዉጭ ግንባር የበላይነት ሥርዓት፤ ግድያ እና የዘረፋ አገዛዝ በአስቸኳይ ያከትም!!

5 እነ እስክንድር ነጋ፤ አንዷለም አራጌ፤ ተመስገን ደሳለኝ ከዓመታት እንግልት በኋላ ተፈትተዉ ሰንደቅ አላማ ከቤታቸዉ በመገኘትበዛሬዉ እለት 12 የታሰሩት ኢትዮጵያዊያን በአስቸኳይ ይፈቱ

6 ከዳር እስከዳር ሁሉን ኢትዮጵያዉያን ያካተተ፤ ወታደሩን፤ ፖሊሲን የጨመረ ታላቅ የሕዝባዊ የማዕበል ተቃዉሞ በአስቸኳይ!!!

7 ህዝቡ በያለበት እራሱን የመከላከል እርምጃ ይዉሰድ።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!!